





# AMARICO

**ኮሮና ቪሩስ ምንድን ነው?**
ኮሮና ቪሩስ በጣም ብዛት ያለው ቫይረስ ሲሆን በእንስሳና በሰው ላይ ከባድ የጤና ችግርን ያስከትላሉ። በሰው ላይ ኮሮና ቪሩስ ከተለመደው የጉንፉን በሽታ በተለየ ሁኔታ በጣም ከባድ በተንፈሻ ኣካል ላይ ኢንፎክሽን ይፈጥራል።

**COVID-19 ምንድን ነወ?**
COVID-19 ማለት በቅርቡ የታወቀ ተላላፊ በሽታ ቫይረስ ነው። “CO” ኮሮናን ያመለክታል ፣ “VI” ማለት ቫይረሱን ሲሆን “19” ደግሞ የታየበት ዓመተ ምህረት ነው።ይህ ኮሮና ቪሩስ እስከ ታህሳስ መጨረሻ 2019 ድረስ በቻይና ውሓም በሚባል ከተማ አልታወቀም ነበር።

**COVID-19 ምልክቶች ምንድን ናቸው?**
የኮሮና ቪሩስ የተለመዱት ምልክቶች ትኩሳት፣ድካም እና ደረቅ ሳል ናቸው።በተጨማሪ በሳንባ መተንፈሻ ላይ ኢንፌክሽን በመፍጠር እስከ ሞት ደረጃ ያደርሳል።

**ለኮሮና ቪሩስ COVID-19 ክትባት፣መድሓኒት ወይም ህክምና ኣለውን?**
ኮሮና ቪሩስ እስከ አሁን ድረስ ምንም ዓይነት ክትባትም ሆነ መድሓኒት አልተገኘለትም፤ሆኖም ግን በበሽታው ለተጠቁት ሰዎች ህመሙን ለማስታገስ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል።ከባድ ህመም ያለባቸው ሰዋች ሆስፒታል መተኛት አለባቸው።በዚህ በሽታ የተያዙ ሰዎች በሚደረግላቸው ህክምና የሚድኑም አሉ።ለዚህ በሽታ ክትባቱን ወይም መድሓኒቱን ለማግኘት በትጋት በመስራት ላይ ይገኛሉ።

**ለኮሮና ቪሩስ COVID-19 በቀላሉ ሊያጠቃ የሚችለው ማንን ነው?**
ኮሮና ቪሩስ በቀላሉ ሊስፉፉና ሊያጠቃቸው የሚችለው ለሽማግሌዎችና አሮጊቶች እንዲሁም ከዚህ በፊት የጤና ችግር ላላባቸው ማለት እንደ ከፍተኛ የደም ግፊት ፣ የልብ በሽታ፣የሳንባ በሽታ፣የካንሰር በሽታና የስኳር በሽታ ያላቸውን ሰዎች በቀላሉ ይጠቃሉ።

IOM
UN MIGRATION

**እራሴን ለመከላከል ከዚህ በሽታ ቫይረስ እንዳይስፉፉ ምን ማድረግ አለብኝ?**

ከኮሮና ቪሩስ ከመያዝ አንዳንድ ቀላል ጥንቃቄዎችን በማድረግ መቀነስ ይችላሉ፥

- እጅን በደምድ አድርጎ በጥንቃቄ በአልኮል በተሰራ የቫይረስ መግደያ ጄል አድርጎ መቀባት፤ እንዲሁም እጅን በደምድ አድርጎ በውሓና በሳሙና መታጠብ ያስፈልጋል ምክንያቱም በእጃችን ላይ ያለውን ቫይረስ ይገድልናል።



- ከሰዎች ጋር ቢያንስ አንድ ሜትር ወይም 3 እርምጃ እርቀት ሊኖረን ይገባል።ቫይረሱ በምራቃችን ነጠብጣቦች ውስጥ ሊኖር ይችላል እንዲሁም በትንፉሽ፣ አየር በማይንቀሳቀስበት ቦታ በቀላሉ ይተላለፋል ምልክቱም ማስነጠስ እና ትኩሳት ናቸው።



- በተቻለ መጠን አይናችንን ፣ አፍንጫችንንና አፋችንን አለመንካት ምክንያቱም መእጃችን ብዙ ነገር ስለምንነካ ቫይረሱን በእጃችን ልናነሳው ስለምንችል።አንድ ጊዜ ከተበከለ እጃችን ቫይረሱን በቀላሉ ወደ አይናችን፣አፍንጫችንንና አፋችንን በመግባት በሽታው ሰውነታችን ውስጥ በመግባት እንታመማለን።

- እርሶ እና አካባቢዎ ያሉ ሰዎችን ያተነፋፈስ ስነስርዓት ንፅህናን ያስታውሉ፤ይህ ማለት አፋዎንና እና አፍንጫዎትን መሸፈንና በሚያስነጥሱበት ጊዜ በእጃችን ክንድ በመጠምዘዣው በማስነጠስ ወይም አንድ ጊዜ የተጠቀሙበትን ሶፍት ወረቀት መጣል። ለምን? ነጠብጣብ ቫይረሶችን በአካባቢዎ ያሉትን ሰዎች እንደ ጉንፋንና ኮሮና ቪሩስ እንዳናስተላልፉ ይጠቅማል።



- በተቻለህ መጠን በእጅ ሰላም ማለትንና መተቃቀፍን ተው፤ምክንያቱም ከላይ በተገለፀው መሰረት፤በተቻለህ መጠን ከቤታችን እንዳንወጣ፣በባለስልጣኑ የሚወጡትን ህጎች መከተል።ትኩሳት፣ሳል ወይም የመተንፈስ ችግር ካሎቦት ባስቸኳይ ወደ ሓኪሞ አስቀድሞ ስልክ መደወል።ይህ ለእርስዎ በአስቸኮይ ሚያስፈልጎትን ትክክለኛ ህክምና እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ይህ ጥንቃቄ ለእርስዎ እና ወደ ሌላ ሰዎች ቫይረሱ እንዳይስፋፋ ይረዳል።



All the measures included in the present leaflet follow what established by the world health organization (WHO)